

# የችግረኛውንም ሕዝቤን ፍርድ

«መበለቶችም ቅሚያቸው እንዲሆኑ፥ ድሀ አደጎችንም ብዝበዛቸው እንዲያደርጉ፥ የድሀውን ፍርድ ያጣምሙ ዘንድ፥ የችግረኛውንም ሕዝቤን ፍርድ ያጐድሉ ዘንድ የግፍን ትእዛዛት ለሚያዝዙ፥ ክፋንም ጽሕፈት ለሚጽፉ ወዮላቸው!»

ትንቢተ ኢሳያስ 10፡ 1-2

በተለይ እግዚአብሔርን እናውቃለን ብለን፣ ለወገን፣ ለአገር፣ ለሰው ልጅ መከራ እና መብት መሙዋገትን ፖለቲካ ነውና አትንኩት እያልን፣ ራሳችንን በአያገባንም ጎራ ውስጥ ከትተን፣ መውጣት ላቃተን ሁሉ እግዚአብሔር መንፈሳችንን ያባንነው ዘንድ ጸሎቴ ነው።

የሕዝባችን መከራ ከምንግዜውም በላይ እጅግ በከፋበት ወቅት በመንፈሳዊ ካባ ራሳችንን



ከልለን በዝምታ መቀመጥ እግዚአብሔር ይጸየፈዋልና፡፡

ጥያቄው ፖለቲከኛ ሁኑ ማለት አይደለም፣ እኔ እስከሚገባኝ ፖለቲካ ማለት በሐቅ እና በእውነት ላይ የተመሰረተ ሕብረተሰብን የማስተዳደር ጥበብ ይመስለኛል፣ ምናልባትም ለአብዛኞቻችን ይህ ቃል የሚዘገንንን፣ ፖለቲካ ማለት ምን እንደሆነ እንኳዋን ጠንቅቀው በማያውቁ ሰዎች ትውልድ አገራችን መመራትዋና፣ በእነርሱም መሐል ማሰተዋል ያላቸው፣ እውቅትን የተሞሉ፣ ምሁራን እና የፖለቲካው እውቀት ያላቸው አማካሪዎቻቸው፣ በየጊዜው የሚሰጡዋቸውን ምክር ያለመስማት እና ከእኛ በላይ አዋቂ ማንም የለም ባይነት፣ አምባገነንነት፣ ጉልበተኛነት፣ ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም በሕዝባችን ሥነልቦና ላይ ያስከተለው ጠባሳ እና የፖለቲካው መዘዝ ያሳረፈበት ሰቆቃ ይመስለኛል ለቃሉ ከፍተኛ ፍርሐት ያሳደረብን፡፡

እኔ በግሌ ከሁለት አስርተ አመታት በላይ የተለየሁዋትን አገር፣ ሁኔታ ላለማወቅ እና ላለመስማት ወስኜ፣ ራሴን ከሁሉ አርቄ የኖርኩ ነበርኩ፣ ለቃሉ ጥላቻ እና ፍራቻ የነበረኝ ሰው ነበርኩ፣ እግዚአበሔር በፈቀደው ጊዜ

ለትውልድ ፈውስ ለማምጣት በተነሳው አገልግሎቴ ምክንያት ባላሰብኩት እና ባልገምተኩት መንገድ እግዚአብሔር ስለ አገር እና ስለ ወገን እንድሰማ ፈቅዶ፣ ከከረምኩበት ድንዛዜ ፈውሶ አባነነኝ፣ ሁኔታዎችን ሚዛናቸውን በጠበቀ መልኩ በሚገባ ለመረዳት መረጃ መሰብሰብ ከጀመርኩ ቅርብ ጊዜ ቢሆንም፣ በዚህ አጭር ጊዜ በሰበሰበኩት መረጃ ብቻ ተነስቼ ፖለቲከኛ ልሁን ብል አያምርብኝም፣ በማላወቀው ነገር መዳከር እንዳይሆንብኝ እና የህይወቴ ጥሪ ባልሆነበት መንገድም ላይ እንዳልሄድ ስለምፈራ ብቻ፡፡

ነገር ግን ሰለ ሕዝቤ መከራ እና ችግር መሙዋገቴን ግን የእግዚአበሔርም ቃል ያግዘኛል፣ አርሱ የፈጠረልኝም ሕሊናዬም፣ የትውልድ እናትነቴም ግድ ይለኛል፣ አካሄዴ ለአንዳንዱ እምነቴን ጥዬ ፖለቲከኛ እንደሆንኩ በማሰብ በፍርሐት ውስጥ እንዳሉ አያለሁ፣ ከዚህ ፍርሐት ባርነት ግን ልንፈወስ ይገባናል፡፡

በሐገርም በስደት ምድርም በሕዝባችን ላይ የሚደርሰውን መከራ፣ በፖለቲከኞች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ እኛም ስለወገን እና ስለሰብአዊነት ግድ ሊለን ይገባል ፡፡ ችግሩ በተቃዋሚዎች እየተጋነነ ነው፣ ሐገሪቱዋ ልማት በልማት

ሆናለች ለሚሉም ቢሆን አገሪቱዋም ሆነ ህዝቡ ሁሉ ደልቶት ቢኖር እና፣ ችግር የደረሰበት እንድ ሰው ብቻ ቢሆን እንኳዋን፣ ስለዛ ሰው መከራ እና ስቃይ ግድ ሊለን ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ፍርድንና ጽድቅን አድርጉ የተበዘበዘውንም ከአስጨናቂው እጅ አድኑ መጻተኛውንና ድሀ አደጉን መበለቲቱንም አትበድሉ፥ አታምፁባቸውም፥ በዚህም ስፍራ ንጹሕ ደምን አታፍስሱ።ትንቢተ ኤርምያስ 22‹3

የተበዘበዘውንም ከአስጨናቂው እጅ ለማዳን የማንችል እና አቅምም ብቃቱም የሌለን ደግሞ፣ ቢያንስ የህዝቡን መከራ ለመታደግ ቀን እና ሌሊት፣ አቅማቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ገንዘባቸውነ፣ ጊዜያቸውን ትዳራቸውን መስዋእት እያደረጉ፣ ለወገን ችግር ለመድረስ የሚተጉትን መንቀፍ ብንተው፣ ያ ራሱ ወገንን ማገዝ ነው፡፡ ክርስቶስም የሞተው እኮ ለሰው ልጆች ሲል ነውና፣ እግዚአበሔርን እናምናለን ብለን እምነታችን በስራ ካልተገለጠ፣ ማመኑንማ አጋንንትም ያምናሉ፣ «እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት

ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።» ይላል
የአምላካችን ቃል በየያዕቆብ መልእክት2›19

አንዳንዶች በአገር ቤት የሚሰሩዋቸው ቤቶች
እና እና አገሪቱዋን ለማልማት እና ለመገንባት
መጣሩ፣ በመልካም እና በቅንነት የተሰራ
ከሆነ፣ ድሐ ደጉ እየተፈናቀለ ካልሆነ፣ የግፍ
እጅ ከሌለበት መልካም ነው፣ መልካም
የማይሆነው ግን ድሐ ደጉን እያፈናቀለ፣
በግፍ፣ በጉቦና በምማለጃ ከሆነ ግን፣ እኛ
እንኩዋን በቀጥታ ባናደርገውም፣
የእግዚአበሔር ቃል ግን ለድሐው
ስለሚሙዋገት እንዲህ ይለናል‹ «ድሀውንም
ደብድባችኋልና፥ የስንዴውንም ቀረጥ ከእርሱ
ወስዳችኋልና ከተጠረበ ድንጋይ ቤቶችን
ሠርታችኋል፥ ነገር ግን አትቀመጡባቸውም
ያማሩ የወይን ቦታዎች ተክላችኋል፥ ነገር ግን
ከወይን ጠጃቸው አትጠጡም።» ትንቢተ
አሞጽ 5‹11 ይለናልና ከማልማቱ ባሻገር ለድሐ
አደጉም መሙዋገቱንም ችላ ባንለው መልካም
ይመስለኛል፡፡

ሁላችን በሕይወት ዘመናችን እንሳሳታልን፣
ልናጠፋ እንችላለን፣ ከስህተት ተመልሰን ንስሀ
መግባት እና ይቅርታ መጠየቅ ደግሞ
በእግዚአበሔርም በሰውም ዘንድ መልካም
ነውና ሁላችንን ይህን አቅም ይስጠን?

ምክንያቱም ለእኛ ተራ የሚደርስልን አይኖርም እና‹» የድሀውን ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደፍን ሰው፥ እርሱ ራሱ ይጮኻል አይሰማለትምም።» ይላል ምሳሌ 21‹13

በሕዝባችን እና በምድራችን ላይ ለበርካታ አመታት ያለፈው መከራ፣ ቂምና በቀል፣ የጣለብን ቁስል ሳይፈወስ በላይ በላዩ በራሳችንም በሕዝባችንም ላይ ሰቆቃን አናበዛ፣ ያፈጠጠውንም እውነት ለእኛ ስላልተመቸን ብቻ እንደሌለ አድርገን እንቁጠር አንካደውም፣

የሰው ልጅ አቅም በፈቅደ ሁሉ ከአምላኩ ጋር፣ ከራሱ ጋር እና ከወንድሙ ጋር ሊታረቅ ይገባዋል ብዬ አምናለሁ፡፡ በትውልድ መካከል እውነተኛ እርቅ ማምጣትም ያስፈልጋል እና ለዚያ ደግሞ ጥርጊያ መንገድ ማመቻቸት አለብን ስንል፣ በታራቂዎች መሐል የተበዳይን አቤቱታ ደብቅን፣ የበዳይንም በደል ሸፍነን ግን ሊሆን አይገባውም ፡፡ ይህ አካሄድ ምናልባትም ለእንድ ወገን ያጋደለ ሊያስመስል ይችል ይሆናል፣ ነገር ግን ፈውስ የሚመጣው እርስ በእርሳችን እውነትን ስንነጋገር ነውና፣ መከራውን ሳነሸፍን፣ » ሁሉን ትታችሁ እና እረስታችሁ በቃ ታረቁ» ብቻ ማለት ሳይሆን፣

በዳዩን የበደልከው ይሄ ነው፣ ለበደልህ በሰማይም በምድርም ፊት ንስሀ ገባ፣ ለበደልከው ክፍል ደግሞ የበደል ካሳ ክፈል ብለን ለመናገር መድፈር አለብን ብዬ በግሌ አምናለሁ፡፡

እኛም እርስ በእርሳችን የበደልንውን ይቅርታ በመጠየቅ ፣ የበደሉንንም ይቅርታ በማድረግ በግላችን ለራሳችን ፈውስን ለማምጣት የተዘጋጀ ልብ እንዲኖረን ጸጋን መለመን ያስፈልገናል፣ ይህን ስል ግን ጥፋተኞች በሕግ አግባብ ለፍርድ ሊቀርቡ የምድርም የሰማይም ሕግ ግድ ስለሚል፣ ይህን ለሕግ ባለሙያዎች ትተን፣ በቤተሰብ፣ በሕብረተሰብ፣ በአገር አቅፍ ደረጃም ብሔራዊ እርቅ ለማምጣት፣ በተለይም እኛ በስደት ምድር ያለን ሰዎች፣ ከአገር ውስጥ መከራ፣ ችግር፣ እስራት፣ ከበረሐ ስቃይ፣ ከባሕር ማዕበል፣ በየቦታው በወሲባዊ ጥቃት በመደፈር…ወዘተ ተርፎ እዚህ የደረሰውን ስደተኛ ሕዝብ ቢቻል በጋራ በተባበረ ክንድ በተግባር ከመከራው ጎን ቆመን፣ ባይቻለን አጽናነተን፣ ቁስሉን አክመን፣ የተሰበረ ልቡን ጠግነን እኛ ራሳችን ካለፍንበት መከራ እና ስቃይ በተጽናናንበት መጽናናት ሌላውን

ለማጽናናት አቅማችንን ሰብስበን፣ ሁላችን በምንችለው ሁሉ እንድንረባረብ እጆቻንንም ልባችንም በጋራ አያይዘን ለመልካም ነገር ሁሉ እንድንተጋ እርስ በእርሳችን ልንበረታታ ያስፈልገናል፡፡

በምንኖርበት በስደት ምድርም ቢሆን ሁላችን በግል ፖለቲካዊ፣ ሕይማኖታዊ፣ ማሕበራዊ ፣ ጎሳዊ.... ወዘተ ጎራ ( ጌቶ) ውስጥ ሆነን፣ ሌላውን ንቀን፣ ያውም ለዛውም ጌቶው ፈቃደኛ ሆኖ ያካተታቸውን ብቻ እንጂ፣ ለእኛ ጌቶ አትመጥንም ተብሎ የተገለለውን ወይም ራሱን ያገለለውን ሳይጨመር፣ በነጻነት ምድር፣ በፍርሐት እስራት ውስጥ ገብተን፣ በአገር ካለው ችግር ባላተናነሰ መልኩ፣ በባዕድ ምድር እርስ በእርስ በጠላትነት እየተያየን፣ ወገን ወገኑን አየሰለለ፣ ወይም እሰለላለሁ እያለ እየፈራ፣ በሥነልቦና እስር ቤት ውስጥ የታጎረውን ቤት ይቁጠረው፡፡

ይህን እያወቅን፣ እየሰማን እያየን ደግሞ፣ ያለንንን እውቅት እና ችሎታ እርሰ በእርሳችን እተከፋፈልን በፍቅር፣ በእንግዳ ተቀባይነት፣ በመተዛዘን፣ በመከባበር የተገነባውን ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ተዘርፎብን፣ ወደን ወይም ተገደን አዘርፍን፣ መቀመጡ፣ በግል ለራሳችን፣ በጋራ ለትውልድ አገራችን፣

በእንግድነትም ለተቀመጥንበት ምድር አይበጅምና ፈውስ ያስፈልገናል፣ ምንም እንኳዋን የሁኔታዎች አለመመቻቸት አንገታችንን ብንደፋ፣ ላለንበትም ምድር፣ ለወጣንበትም ምድር የሚተርፍ የባለ ብዙ እውቅት እና ችሎታ ባለቤቶች የሆንን ሕዝብ እንደሆንን አምናለሁ፡፡ ስለዚህ ለመልካም ስራ እንነቃቃ ለትውልድም ለምድራችንም ለተሰደድንበትት ምድር እንትረፍ፣በልተን ጠጥተን፣ ምድርን ስንሰናበት ተከትሎን የማየሄደውን፣ ዝናን፣ ስልጣን፣ ሀብት፣ ቅራቅንቦን ሰብሰበን እንቅመጥ፣ ማናችንም ከማንም አናነስም አንበልጠምም፣ ሁላችን በፈጣሪ አምሳል የተፈጠረን ክቡር የሰው ለጆች ነንና፡፡

በሕዝባችን ላይ በአገርም በስደት ምድርም ወገን፣ ቤተሰባቸውን ላጡ ወገኖቻችን ሁሉ የእግዚአብሔር መጽናናት ከእነርሱ ጋር ይሁን፣ ለእኛም የቆምን ለምንመስል፣ ከራስ ወዳድነት በሽታ ፈውሶን ለወገኖቻችን፣ ለእርስ በእርሳችንም መፍትሔ አመነጪ ያድርገን! «እኔ ምን ማድረግ እችላለሁ?» ብለን ከተደቀበቅንበት አቅመ ቢስነት ጎራ ወጠተን፣ በግል ማድረግ የምንችለውን በግል ፣ በጋራ ደግሞ ምንም ያህል ደካማና አቅመቢስ ብንሆን

እንኩዋን ብርቱዎች ልንሆን እንደምንችል አውቅን እንያያዝ፣ የምንያያዘው፣ አንድ አይነት ፖለቲካዊ፣ ሐይማኖታዊ ወይም ማሕበራዊ አመለካከት ስላለን ሳይሆን፣ ኢትዮጵያ ከምትባል ምድር እንደመጣን ሰብአዊ ፍጡር፣ የትውልድ አገራችን ምድር ጉዳይ ያገባናል፣ የህዝባችን መከራም ይሁን ደስታም ያገባናል፣ የሚል ስሜትን ልናነቃቃው ይገባናል ብዬ አምናለሁ፣ ይህ ደግሞ ሁላችንንም ይጠቅመናል እነጂ አይጎዳንም ለዚህም ጌታም ይርዳን፡፡ ልዑል እግዚአብሔር ምድራችንን፣ ሕዝባችንን እና እኛንም በባእድ ምድር ያለንውን ጭምር ይፈውሰን አሜን፡፡

ከዚህ በታች ያለውን ኢትዮጵያ ብትመች? ግጥም ከProfessor Fikre Tolosa http://www.ethiomedia.com/100leads/ethiopia_bitimech.pdf

እንዲያነቡ እየጋበዝከዎ የምሰናበትዎ ትውልደ ኢትዮጵያዊት እናት ከሰሜን ዋልታ ስር ካለች የገጠር መንደር፣ በቸር ያገናኘን፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር

**ሰዋስው ስለሺ ዮሐነሰን**
The Ark of the New Covenant Healing Ministry www.adonairapha.org
mail@adonairapha.org
12.05.2015